የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

# ፋኖ

*<u>ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት</u>*

*<u>ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ</u>*

*<u>ለአርሲ ሕዝባችን የተሰጠ ድጋፍ</u>*

## ካለፈው ስሕተትአለመማር !!

ሰው የጀመረውን ዓላማ ከግብ ማድረስ የሚችለው ካለፈው ሥራው መማር ሲችል ነው።ያለፈው ድርጊት ውጤቱ የሰመረ ከሆነ አሻሽሎ መቀጠል፣ ዉድቀትም ከሆነ ደግሞ አለመድገም ከግብ ያደርሳል።ለዚህ ነው አባቶች ሲተርቱ....ከዉድቀቱ የማይማር ሬሳ ብቻ ነው....የሚሉት፣ የፖለቲካ ሥራ ወይም ሕዝብን ማስተዳደር ራሱን የቻለ ፈሊጥ ወይም ዘዴ አለው። የሕዝብ ፍላጎት ከዕለት ወደ ዕለት እንደሚቀየር ሁሉ የአመራር ስልትም እንደወቅቱ ይሄዳል፣ለዚህ ነው በሰለጠኑት አገሮች ምርጫ ላይ ተወዳዳሪዎች አዳዲስ ሐሳብ ሰንቀው ወደ ሕዝባቸው የሚቀርቡት።

የኦሕንኢአ ብቸኛ የአንድነት መርሃ ግብር ያለው መሆኑን ማንም ኢትዮጵያዊ ጠንቅቆ የሚያውቀው ነው፣አንድነት መፈለጉ ጥቅሙ ለኦሮሞ ሕዝብ እንጂ ሌላውን ለማስደሰት ወይም ኦሮሞን አሳልፎ ለመስጠት አይደለም።ዛሬ በቦታው የሚገደለው፣ የሚፈናቀለውና የሚሰደደው አንድነት በመታጣቱ ነው፡

የአንድ አገር ሉዓላዊነቱ የሚከበረው አንድነት ሲኖር ነው።የኦሮሞ ነፃነት ትግል ከጀመረ ረጅም ጊዜ ቢያስቆጥርም ትግሉ እንደተጀመረ ወደፊት የገፋው በወራት በሚቆጠሩት ጊዜ ነው። ሦስት ወር ያልሞላው የኦሮሞ ደሞክራስያዊ ፓርቲ ከጅምሩ የኦሮሞን ሕዝብ እየጎድው ነው፡ብዙም ሩቅ ሣንሄድ በአርሲ ኦሮሞዎች ላይ በመፈፀም ላይ የሚገኘው ታሪክ ይቅር የማይለው በደል መጥቀሱ በቂ ነው። ስለሆነም የአርሲ ሕዝብ በመሰባሰብ ብሦቱንና ምሬቱን በአደባባይ ሲገልፅ የሚያሳይ ቪዲዮ አባሪ አድርገን ([https://m.facebook.com/100009178472149/posts/2161697444146184/](https://m.facebook.com/100009178472149/posts/2161697444146184/) የኦሮሞ ሕዝባችን ብቻ ሣይሆን መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲመለከትና አስተያየት እንዲሰጥበት አሰራጭናል። የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ በጋራ በመሆን ለአርሲ ሕዝባችን የድጋፍ ድምፃቸውን ያሰሙት ሕዝቡ በቂዬው በደል ደርሶ በማየታቸው ነው፣ የአርሲ ሕዝባችን ብሶታቸውን ሲያሰሙ ከመስማታችንም ባሻገር በርካታ በተሰብ እንደተጎዳ በማየታችን ለተጎጂ በተሰቦች መፅናናትን ስንመኝ ለወደፊቱ የአርሲ ሕዝብ ራሳቸውን ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከጎናቸው መሆናችንን እየገለጽን፣ የአርሲ አባገዳዎች የሰጡትን መመሪያ ያለምንም ማመንታት መቀበላችንና ለአባሎቻችን እንደምንገልጽ ቃል እንገባለን !!

[https://m.facebook.com/100009178472149/posts/2161697444146184/](https://m.facebook.com/100009178472149/posts/2161697444146184/)

ኢትዮጵያ ለአስመሳዮች መሸሸጊያ አትሆንም !!

አንድነታችን ለዘለዓለም ለምልሞና አብቦ ይኖራል !!

| | |
|---|---|
| ኢሕብፓ EPNP የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY | ኦሕንኢአ OPMEU |

EPNP.INFO